የስቴት ትምህርት የበላይ
ተቆጣጣሪ ቢሮ

# የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ቤት እና የተስፋፋ የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ቤት ሰራተኛ ብቁነት መስፈርቶች በስራ መደብ

## የዲሲ የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ ለመሆን የብቁነት መስፈርቶች

ከዲሴምበር 2023 ጀምሮ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ፈቃድ ያለው የልጅ እድገት ማዕከል ውስጥ **የቤት ውስጥ ተንከባካቢ** የሆነ ሰው ከታች ያሉ **<u>ሁለቱን</u>** የምስክር ወረቀቶች መያዝ አለበት፦

1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙ፤ **እና**
2. የልጅ እድገት ተባባሪ (CDA) የምስክር ወረቀት።

ሰንጠረዥ 1 አሁን ያለውን የቤት ውስጥ ተንከባካቢ የትምህርት መስፈርትን በዲሴምበር 2023 ውስጥ ተግባራዊ ከሚሆነው አዲሱ መስፈርት ጋር ያነጻጽራል።

**ሰንጠረዥ 1**

| የሚያስፈልገው ያሁኑ የትምህርት የምስክር ወረቀት | በዲሴምበር 2023 የሚያስፈልገው አዲስ የትምህርት የምስክር ወረቀት |
|---|---|
| • የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙ | • የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙ፤ **እና**<br>• የCDA የምስክር ወረቀት፣ |

## የዲሲ የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ ለመሆን የብቁነት መስፈርቶች

ከዲሴምበር 2023 ጀምሮ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ፈቃድ ያለው የልጅ እድገት ማዕከል ውስጥ **የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ** የሆነ ሰው ከታች ካሉት የምስክር ወረቀቶች**<u>አንዱን</u>** መያዝ አለበት፦

1. ተባባሪ ዲግሪ በቅድመ ልጅነት ትምህርት፣ የቅድመ ልጅነት እድገት፣ የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች ወይም በቅርብ ተዛማጅነት ባለው ፊልድ/መስክ፤ **<u>ወይም</u>**
2. ቢያንስ 24 የሴምስቴር ክሬዲት ሰዓታት ባለው በቅድመ የልጅነት ትምህርት (ኤርሊ ጃይልድሁድ ኢዱኬሽን) ተባባሪ ዲግሪ እና ከልጆች ጋር በመስራት የአንድ ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት የስራ ልምድ

ሰንጠረዥ 3 አሁን ያለውን የተስፋፋ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ የትምህርት መስፈርትን በዲሴምበር 2023 ውስጥ ተግባራዊ ከሚሆነው አዲሱ መስፈርት ጋር ያነጻጽራል።

**ሰንጠረዥ 2**

| የሚያስፈልገው ያሁኑ የትምህርት የምስክር ወረቀት | በዲሴምበር 2023 የሚያስፈልገው አዲስ የትምህርት የምስክር ወረቀት |
|---|---|
| • በቅድመ ልጅነት ትምህርት 15 የሴምስተር ሰዓታት ያለው 48 የሴምስተር ክሬዲት ሰዓታት እና የ2 ዓመት ቁጥጥር የተደረገበት የስራ ልምድ **<u>ወይም</u>** የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ እና ያሁኑ የልጅ እድገት ተባባሪ (ቻይልድ ዲቬሎፕመንት አሶሲየት (CDA)) የምስክር ወረቀት/ማረጋገጫ | • ተባባሪ ዲግሪ በቅድመ ልጅነት ትምህርት፣ የቅድመ ልጅነት እድገት፣ የልጅ እና የቤተሰብ ጥናቶች ወይም በቅርብ ተዛማጅነት ባለው ፊልድ/መስክ<br>**ወይም**<br>• ተባባሪ ዲግሪ (ወይም ከዚያ በላይ) በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ፣ ቢያንስ በቅድመ ልጅነት ትምህርት የ24 የሴምስቴር ክሬዲት ሰዓታት ያለው |

## የዲሲ የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ ተባባሪ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ ለመሆን የብቁነት መስፈርቶች

ከዲሴምበር 2023 ጀምሮ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ፈቃድ ያለው የልጅ እድገት ማዕከል ውስጥ **ተባባሪ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ** የሆነ ሰው ከታች ያሉ **ሁለቱን** የምስክር ወረቀቶች መያዝ አለበት፥

1. የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙ፤ **እና**
2. የልጅ እድገት ተባባሪ (CDA) የምስክር ወረቀት።

ሰንጠረዥ 2 አሁን ያለውን ተባባሪ የቤት ውስጥ ተንከባካቢ የትምህርት መስፈርትን በዲሴምበር 2023 ውስጥ ተግባራዊ ከሚሆነው አዲሱ መስፈርት ጋር ያነጻጽራል።

**ሰንጠረዥ 3**

| የሚያስፈልገው ያሁኑ የትምህርት የምስክር ወረቀት | በዲሴምበር 2023 የሚያስፈልገው አዲስ የትምህርት የምስክር ወረቀት |
|---|---|
| • የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙ | • የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም ተመዛዛኙ፤ እና<br>• የCDA የምስክር ወረቀት |

## መስፈርቶችን ማሟላት ላይ ድጋፍ ይፈልጋሉ?

እነዚህን መስፈርቶች ለማሟላት ድጋፍ ካስፈለገዎ፣ የስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (ኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን) (OSSE)፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዩኒቨርሲቲ እና በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ሌሎች ኮሌጆች እና የህብረተሰብ ድርጅቶች ዲግሪ እንዲያገኙ የሚያግዙዎት የተለያዩየስልጠና እና የስኮላርሺፕ ፕሮግራሞችን ያቀርባሉ። እርስዎ አሁንም ትምህርትዎን እየተማሩ ከሆነ ወይም ካልሆነ እስከ ዲሴምበር 2023 መስፈርቶቹን ሙሉ በሙሉ የማያሟሉ ከሆነ፣ የእርስዎ የተቋም ባለቤት እርስዎን ወክሎ ለአጠቃላይ መታለፍ ማመልከት ይችላል። በተጨማሪም፣ ላለፉት 10 ዓመታት (ከዲሴምበር 2006 ወይም ከዚያ በፊት ጀምረው) በተመሳሳይ (ወይም ተነጻጻሪ) ሚና/የስራ መደብ ላይ በአገልግሎት ላይ ጉልህ ክፍተት ሳይፈጥሩ በቀጣይነት አገልግለው ከሆነ፣ የእርስዎ የተቋም ባለቤት ለ 10-ዓመት ተከታታይ አገልግሎት መታለፍማመልከት ይችላል።

እባክዎ መታለፎች በጉዳይ-ለጉዳይ መሰረት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ እና ዋስትና እንደሌላቸው ያስተውሉ—ስለዚህ በተገኙ የትምህርት እድሎች እንዲጠቀሙ በጥብቅ እናበረታታዎታለን።

የግል እቅድ ለማዘጋጀት እርዳታ ካስፈለገዎ ወይም እንዴት እንደሚጀምሩ እርግጠኛ መሆን ካልቻሉ፣ የECE እርዳታ-ሰጪ የፊት ወንበር ላይ የተቀመጠውን ሰው ያነጋግሩ። ድጋፎች በተለያዩ ቋንቋዎች ይገኛሉ።

### እኛ ድጋፍ ለመስጠት እንገኛለን!

የECE እርዳታ-ሰጪ የፊት ወንበር ላይ የተቀመጠ ሰው የመገኛ መረጃ፥ ECEhelpdesk@dc.gov ወይም (202) 478-5903

| በአስፈላጊነት የሚገኝ | በቀጠሮ |
|---|---|
| ይደውሉ ወይም ኢሜይል ይላኩ እና ምላሽን ወዲያውኑ ወይም በ24 ሰዓታት ውስጥ ይቀበሉ | የግል የመገኘት ሁኔታዎ ላይ በመመርኮዝ ለግላዊ እቅድ ቀጠሮ ለመያዝ ይደውሉ ወይም ኢሜይል ይላኩ |